# የመለስ አገዛዝ እና የሚድያ ማምታታት
# (Misinformation and Disinformation)

የመለስ አገዛዝ የፕሬስ ነጻነትን ማፈን (መከልከል) ብቻ ሳይሆን ህዝብን በማምታታት (በ **Misinformation and Disinformation**) የተካነም ነው። አንዳንዶቹን በየሜዲያው የሚለቀቁትን ጽሁፎች ላስተዋለ ሰው፣ አገዛዙን ከሚያወግዙ ስዎች አቅጣጫ የተጻፉ የሚመስሉ (አገዛዙን ብዙም የማይጎዱ፣ አንዳንዴም ከተራ ስድብ ያላለፉ) ተቃዋሚውን ድርጅትም ሆነ ግለሰብ ኢላማ ያደረጉ ሊሆኑ ይችላሉ።

በቅርቡ "የነፃነት ጎህ ሲቀድ"ን የቃኙልን መስፍን ማሞ ተሰማ፣ ከገለባ ክምር ውስጥ የወደቀ መርፌ የመፈለግ ያህል መከራቸውን ሲያዩ እና ሲያበራዩ ከርመው፣ ከ614 ገጽ መጽሃፍ ውስጥ ያወጡልን የመጽሃፉ ሳንካ፣ ደራሲው "...ፍርዱን ለአንባቢ በመተዋቸው...." እና "እናንተው ፍረዱ..." በማለታቸው ነው። ሌላም አግኝተዋል። መስፍን፣ ከመጽሃፉ ውስጥ ያገኙትን *"ኢህአዴግ የኤርትራን መገንጠል ለማወቅ የመጀመሪያ መሆን ብቻ ሳይሆን በቶሎ እስከትገነጠልለት ድረስ መጠበቅ ያቃተው እስኪመስል ድረስ፤ የኢትዮጵያን ጥቅሞች ከግምት አለማስገባት ወዘተ ተዳምሮ ኢትዮጵያውያን የኢህአዴግን አቋም* ***አልወደዱለትም*** *ለማለት ይቻላል..."* የሚለውን ጠቅሰው፡ "**አልወደዱለትም"** የሚለውንም አፅንዖት ሰጥተው ሲያበቁ፡- ደራሲው ራሳቸውንም በአ፟ኳኋት አንደኛ መደብ ብዙ {1st person plural} ራሳቸውን ጨምረው፣ ለምን **"...አልወደድንለትም"** አላሉም" ብለው ይወቅሷቸዋል።

የመስፍን ማሞን ቅኝት አንድ ሁለት አንቀጽ ያነበበ ሰው፣ የጽሁፉን አቅጣጫ እና ከ*የትነት* ለመገመት የሚሳነው አይመስለኝም። እሱ ብቻም አይደለም። መስፍን ማሞ አማርኛንም እጅግ በጣም የሚያውቁ ሰው ለመምሰል—እረ እንዲያውም እኔ ከዚያ በላይ እወስደዋለሁ— *'ከሌላ ጎሳ የወጣሁ ኢይደለሁም'* ለማለት ይመስላል—የተሟሟቱትን ሞት ለማወቅ እንዲህ ከባድ አይደለም። እስኪ አሁን፣ የ"ፀ"ን ዘር እና እርባታውን ሁሉ በ"ጠ" ዘር እየተኩ "ገጥ"፣ "አንቀጥ" እያሉ መጻፍ ምን ለማለት ሊሆን ይችላል? "ሲድኒ አውስትራሊያ ከኖሩ በጣም ቆይተዋልና..." እንዳይባል፣ ወረድ ብለው ባሉት አንቀጾች ውስጥ፣ የ"ጠ"ን ዘር ረስተው ባግባቡ የ"ጸ"ን ዘር ተጠቅመዋል።

ይህ ጽሁፍ የመስፍን ማሞን ቅኝት ለመቃኘት ያለመ አይደለም። እንኳን መልስ በመጻፍ የማባክነው ጊዜ፣ ለማንበብ ያባከንኩት ጊዜም አሳዝኖኛል። አንድ ጥሩ ነገር ያገኘሁበት ነገር ቢኖር፣ የመለስን አገዛዝ እጅግ የወረደ፣ ግን ደግሞ በጣም አደገኛ እና በተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን የሚወጡ፣ በመለስ የሚድያ ካድሬዎች የሚለቀቁ ጽሁፎችን [በእጅ አዙር ተቃዋሚ መስለው የሚጽፉትን ማለቴ ነው፣ ባደባባይ *'የመለስን አገዛዝ እንደማቱሳላ ያርዝምልን'* የሚሉትን አይደለም]) ባጠቃላይ የሜድያ ስራ ስላስታወሰኝ ነው። የመለስ አገዛዝ የመናገር እና መጻፍ ነጻነትን ከመከልከል፣ በግልጽ እንደ አኬልዳማ የመሳሰሉት ከሰብዐዊነት የወረዱ ስራዎችን ባደባባይ ከመልቀቅ በላይ፣ በእጅ አዙር ህዝብን በሜድያ ማደናገር እና ማወናበድም ያውቅበታል።

ይህ የመስፍን ማሞ ጽሁፍ በመለስ የሚድያ ካድሬዎች ቢሮ ተጠናቅሮ የወጣ ጽሁፍ ለመሆኑ ማረጋገጫ ባይኖረኝም፣ ለሃገሩ ቅን በሚያስብ አንድ ዜጋ የተጻፈ አይመስለኝም። ምክንያቶቼ ሁለት ናቸው። አንደኛ የጽሁፉ ውስጣዊ ይዘትና ጭብጥ ነው። ሁለተኛ "እባብ ያየ በልጥ በረየ" እንዲሉ ነው። በ1980ዎቹ አጋማሽ አካባቢ በእፎይታ መጽሄት በፕሮፌሰር አስራት ወልደየስ ስም አንድ ጽሁፍ ይወጣል። *[ይህን አሁን ከዚህ በላይ እኔ የጻፍኳቸው ሁለት አንቀጾች፣ አንባቢ የየራሱን Nth term (ለምሳሌ እያንዳንዱን አምስተኛ/ስድስተኛ ቃል) እያወጣ በመጣል፣ ቀሪውን ጽሁፍ በምናብ ለማንበብ ይሞክር። ምንም እጅና እግሩ የማያስታውቅ ጽሁፍ ነው የሚሆነው]* በፕ/ር አስራት ስም የወጣውም ጽሁፍ እንደዚያ ነበር። እና ያኔ በጣም አዝኜ "... ኤጭ! እኒህ ሰውዬ አርፈው የተካኑበትን ህክምናቸውን ቢሰሩ ይሻል ነበር...." ለማለት ተገድጄ ነበር። *(እንደዚህ አይነት ጽሁፎች ለጊዜውም ቢሆን የሚያሳድሩትን ስሜት ልብ ይበሉ)* እንኳንስ አማርኛ ያፍ መፍቻ ቋንቋው የሆን፣ ኣማርኛ እየተናገረ ሰሜን ሸዋ ውስጥ ያደገ፣ በኮሌጅ ደረጃ አማርኛን እንደ ማንኛውም ኮርስ የተማረ ሰው እንደዚያ ያለ አማርኛ ሊጽፍ እንደማይችል እንዴት እንዳላሰብኩ አሁን ድረስ ይገርመኛል። ቆይቶ ቆይቶ፣ የመለስ አገዛዝ የደህንነት እና የሜድያ ሰዎች ስራ መሆኑ የገባኝ፣ መለስ ዜናዊ የመንግስቱ ሃ/ማርያምን ጫማ ሲጠርግ የተሳለ ካርቱን፣ በከተማዋ ውስጥ የተሰራጨውን ወረቀት ያዘጋጁትም የበተኑትም የመለስ ሰዎች መሆናቸውን የሚያውቅ ሰው ከነገረኝ በኋላ እና በ1984 አካባቢ ደግሞ "መንግስቱ ሃ/ማ 100ሺ ጦር ይዞ በአምቦ በኩል ወደ አዲስ አበባ እየገሰገሰ ነው" የሚል ዜና ይዘው የወጡ ጋዜጦች፣ በእጅ አዙር በመለስ ደህንነት ሰራተኞች አማካይነት የተሰራ መሆኑን ከውስጥ አዋቂ ከተረዳሁ በኋላ ነበር።

በ1980ዎቹ አጋማሽ አካባቢ፣ አገሪቱ ዲሞክራሲ በዲሞክራሲ ስትሆን የታየው፣ እንደኔ ያለ ተራ ዜጋ (ordinary person) ቁጥሩ ቀላል አልነበረም። ይህ ማለት፣ በጎን እጅግ ከልብ የሆኑ (genuine) የሆኑ ጽሁፎች፣ "እውነትም ዲሞክራሲ እና/ወይም የማንበብና የመጻፍ ነጻነት አለ" ለማለት የሚያስደፍር ሁኔታ አልነበረም አይባልም። አሁን እነ ጦቢያን፣ የአፍሪካ ቀንድ፣ አዲስ ዜና... ወዘተ የመሳሰሉ መጽሄትና ጋዜጦች ላይ ይወጡ የነበሩትን ጽሁፎች ያነበበ *(ነገር ግን የመለስን እና ቡድኑን ውስጣዊ ማንነት ያላወቀ)*፣ በኢህአዴግ ጨርሶ እንዴት ተስፋ ይቆርጣል? ዶ/ር ብርሃኑስ እንደ አንድ ኢትዮጵያዊ በጽሁፍና ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ለማረም ቢሞክሩ ምን ጥፋት ነበረው? መስፍን ማሞ በ"የነጻነት ጎህ ሲቀድ" ውስጥ፡-

"...ኢህአዴግና መሪዎቹ ዘላቂ ጥቅማቸውን ያውቃሉ ከሚል ስሌት ቀስ በቀስ እንዳይደነብሩ በስልት ከተያዙ የዲሞክራሲ ሽግግሩን በሠላማዊ መንገድ ለማድረግ ይተባበራሉ፤ የዓለምን ታሪክ ሂደት ይገነዘባሉ፤እያደር ከዲሞክራሲና ከነፃ ህብረተሰብ ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ይረዳሉ የሚል እምነት ስለነበረኝ ነው። አሁንም 'የአዎንታዊ በሽታ' በሉት እንጂ ሙሉ ለሙሉ ተስፋዬን አልቆረጥኩም"

የሚለውን ጠቅሰው ነው *"አንባቢ ሆይ! 'የነፃነት ጎህ ሲቀድ' ጠሀፊ ይህንን እጅግ አስገራሚ፤ አስደንጋጭና አሳዛኝ አባባል ያሰፈሩት ኢህአዴግ የኢትዮጵያን ህዝብ ድምፅ ማጅራት መትቶ ሌሎች የፖለቲካ መሪዎችን ጨምሮ እሳቸውም የኢህአዴግ ሰለባ ከሆኑበት ቃሊቲ እስር ቤት ውስጥ ሆነው ነው። በ1998 ዓ/ም በግፍ ከታሰሩበት እስር ቤት (ከአስራ አምስት ዓመታት የኢህአዴግ ኢፍትሃዊ አገዛዝ በኋላ) እንኳን በኢህአዴግ ላይ 'አንጀታቸው ሊቆርጥ' አለመቻሉ አስገራሚ አስደንጋጭና አሳዛኝ..."* ነው የሚሉን።

'የነፃነት ጎህ ሲቀድ' ደራሲ በመለስ አገዛዝ ላይ ሊጨክኑ የማይችሉ ናቸው፣ እረ እንዲያውም ውስጥ ውስጡን ለመለስ አገዛዝ የሚሰሩ ሊሆኑ እንደሚችሉ እንድንጠራጠር ሆን ተብሎ የተደከመበት ነው የሚመስለው። እኔ የታየኝ፣ የመስፍን ልፋት ነው--ለዚህ አላማቸው የሚመች ቃላት እና ሃረጋት ፍለጋ ያን ሁሉ ገጽ ስንቱ ደጋግመው አነበቡት?

የተከበሩ ቃኚ መስፍን ሆይ! የመለስ አገዛዝ "ማጅራት መቺ"፣ "ባንዳ"፣ "አገር ሻጭ"፣ "የኤርትራ ጠበቃ ባንዳ"፣ "ዘረኛ" ወዘተ...መሆኑን ማወቅዎ መልካም ነው። ነገር ግን በነዚህ ብዙ በተባለላቸው ጉዳዮች ላይ ተንጠልጥለው፣ የ"ነጻነት ጎህ ሲቀድ" ደራሲን የማሳጣት መልእክት ማስተላለፍ የፈለጉ ነው የሚመስለው። የ"ነጻነት ጎህ ሲቀድ" ደራሲ ደግሞ በኤርትራ ጉዳይ ላይ ያላቸውን አቋም በግልጽ አሳውቀዋል።

በተረፈ በአጠቃላይ በአገራችን ጉዳይ ላይ፣ እንዲያውም *ከወይራ* የጠነከረ ሰብእና እና ሞራል ያላቸው ሰው መሆናቸውንም ጭምር መጽሃፋቸውን አንብበን፣ የሚናገሩትንም ሰምተን፣ በድርጊትም በኢኢዩ በትምህርታቸው በጣም ጎበዝ የሆኑ፣ ነገር ግን በችግር ምክንያት ሊያቋርጡ ይችሉ የነበሩ ተማሪዎችን በመርዳት የሚታወቁ የነበሩ መሆናቸውን የምናውቅ ብዙ ዜጎች አለን። አሁንም እያስመዘገቡት ያለውን ውጤት እያየን ነው። የበረከት "ወይራ ፖለቲከኛነት" እንዲያው ቀልድ ነው። የቁጠማ ያህልም የሰብአዊ ሞራል ብርታት እና ጥንካሬ የላቸውም። ቀድሞ በረሃ እያሉ፣ በልተው እና ሮጠው ያልጠገቡ "ወደ እናቶቻችን መልሱን!"፣ "አንታገልም" ያሉትን የትግራይ ህጻናት፣ እነዚያን እንቦቀቅላዎች በመደዳው ለመግደል የማይራሩ ሰዎች ናቸው። በ1997 ምርጫ፣ እንደ ናሙና፣ ፖሊሶችን እጃቸው ላይ እንደገባ እንዲሁ የገደሉ ናቸው--በብቀላ መልሰው ህዝቡ ላይ እንዲተኩሱ እና እንዲገድሉ። ከዚህ የባሰ ሞራለ-ልፍስፍስ ሰው ከየት ይገኛል?

የመለስ ቡድን የ"disinformation/misinformation) ስትራቴጂ፣ ከድሮ ጀምሮ የነበር እና አሁንም ያለ ነው። አጠገቡ ያሉትን እና የተቃወሙትንም ሁሉ ለማጥመድ፣ ለማስወገዝ፣ ለመወንጀል እና ብሎም ለማጥፋት፣ አስቀድሞ የተጠናበት የ"disinformation/ misinformation) ስራ ያዘጋጃል፣ ያሰራጫል። ከተሃህት ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ፣ የተሻለ አመለካከት ያላቸውን እና የነበራቸውን ሁሉ ሲያስወግዱ እና ሲያጠፉ፣ በሰራዊቱና በህዝብ ማስጠቆር ሲፈልጉ ሁሉ ይጠቀሙበታል። የመስፍን ማሞ ጽሁፍ፣ የመለስን አገዛዝ ስንትና ስንት ጉዳጉድ ሽፋፍኖ፣ ብዙም በማይጎዳና "ማጅራት መቺ.." ከማለት ባላለፈ ቃላት ለኮፍ እያደረጉ፣ ሲፈልጉም መካብ አይሉት መናድ፣ "ወይራ ፖለቲከኛ"፣ "ኢህአዴግ ምላጭ ፖለቲከኛ" ወዘተ እያሉ፣ የ"ነጻነት ጎህ ሲቀድ" ደራሲን ደግሞ ለማስወገዝ ያልፈነቀሉት ዲንጋይ የለም።

## ማሳረጊያ፡-

ሚድያ ሊሰራ የሚችለው ስራ ተዓምር ነው። በቅርቡ የሞቱትን፣ በአምባገነንነታቸው በአለም የሚታወቁትን (በብሄራዊ ስሜታቸው የማይታሙ የነበሩ ቢሆኑም) የሰሜን ኮሪያውን መሪ ኪም ጆንግ ኢልን ሞት አስመልክቶ፣ የህዝቡን ምላሽ--ሰማይ የተደፋባቸው ያህል ሲያለቅሱ--አይተናል። ህዝብ አማራጭ ሚድያ ካላገኘ እንዲህም ሊያስብ ይችላል። በሚገባ የተደራጀ ሚድያ (በአሜሪካ እና አውሮፓዊያኑ እየታገዘም ቢሆን)፣ በአረቡ አለም እስከ ጊዜ ፍጻሜ ድረስ የማይነኩ ይመስሉ የነበሩ አምባገነኖችን የአገዛዝ እድሜ እንዴት እንዳሳጠረ አይተናል።

ሜዲያዎቻችንን በቋሚነት ለማቆየት በገንዘብ፣ በእውቀት፣ በሞራል ወዘተ... ለማገዝ፣ በቤተሰብ ደረጃ፣ ለምሳሌ እያንዳንዱ ሰው በቤተሰብ ደረጃ በቅድሚያ ባል ከሚስት፣ ሚስት ከባል ጋር እንዴት እንደሚሳተፉ እንዲወያዩበት ማድረግ፣ ከዚያ ወደ እህትና ወንድም... ጓደኛ፣ ጎረቤት፣ የቅርብ የስራ ባልደረባ፣ የመ/ቤት ባልደረቦች... ወዘተ እያለ መተማመን እየፈጠረ እንዲነጋገርበት ማድረግና ጥሩ ተሳትፎ እና ድጋፍ ማስባሰብ ይቻላል።

የሚድያ (ፖለቲካ) ስራው ባብዛኛው፣ በሃገር ውስጥ ያለውን ህዝብ ተደራሲ ያደረገ ሊሆን ይገባዋል፣ ወይም ቢያንስ ለሃገር ውስጥ ተደራሲ በተለይ የተዘጋጀ የፖሊቲካ ሜዲያ ስራ ያስፈልጋል። የሚድያ ስራ አካባቢያዊ (Local) ሲሆን ይበልጥ የሚስብ ይሆናል። ስለ እውነት እንነጋገር ከተባለ፣ የመለስ አገዛዝ አንዳንዶቹን ስለ እውነት የሚዘግቡ ጋዜጠኞችን፣ በመሸኛ ደግሶ የመልቀቅ ያህል ነው ካገር እያስወጣ ያለው። የእስክንድር ነጋን እና መሰል ጋዜጠኞችን ሰብእና፣ ብርታት እና ጥንካሬ የምናደንቀውም ለዚህ ነው።

ከሃገር ውጭ ላለውም ተደራሲ እንዲሁ በተለየ መልኩ ቢዘጋጅ የተሻለ ይመስለኛል። በመለስ አገዛዝ በሚደርሰው ግፍ እና በደል ምክንያት የኢትዮጵያ ህዝብ የወደፊት እጣ ፈንታ እያንዳንዱን በውጭ የሚኖር ኢትዮጵያዊ እንዴት ነው *አፌክት* የሚያደርገው? ተስፋየ ለማ የተባሉ አንድ አንጋፋ የኪነት ሰው የጻፉት መጽሃፍ ውስጥ "...በወጣትነቴ ገንዘብ፣ እውቀት እና ጉልበቴን በሰው አገር ላይ ጨርሼ፣ ሳረጅ አገሬ ገብቼ እጦራለሁ፣ ... ስሞት አገሬ ቅበሩኝ' ብል..። ለሃገሬ ምንም ሳልሰራ፣ የኔ የደከመ፣ የበሰበሰ ስጋና አጥንት ምን ይሰራላታል....?" አይነት ጽሁፋቸውን ማንበቤ ትዝ ይለኛል።

የያንዳንዳችን ሰብእና የተለያየ ነው። አንድ ሰው ትክክለኛውን ነገር የሚሰራው ለመታወቅ/ለዝና አይደለም። እንዲሁ ትክክለኛውን ነገር መስራት/ማድረግ ስላለበት እና ስለሚያስደስተውም ነው። ደስታን የሚያገኝበት መንገድ ያ ብቻ ነው። (they just want to do the right thing"፣ እግረ መንገዱን ዝነኛ ሊሆንም ግን ይችላል። አንዷለም፣ እስክንድር ነጋ ወዘተ... እንደማንኛውም ሰው ተሰደው መኖር የሚያቅታቸው አይደሉም፣ እናም የተሻለ ቁሳዊ ህይወትን ሊኖሩ ይችሉ የነበሩ ናቸው።  they just do not want to do it! And they want to do the right thing! እናም በዚህ ደስተኞች ናቸው። የኔሰው ገብሬ፣ እንደ አብዛኞቻችን መደዴ (ordinary) ህይወትን መኖር ይችል ነበር። እየተቃጠለ፣ ግን ደግሞ እየተደሰተ የሞተ ሰው ነው። ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ እና መሰል ሌሎች ሰዎች፣ ምናልባትም አሁን ከሚኖሩት ኑሮ በተሻለ (ቁሳዊ ህይወት) አገር ውስጥ መኖር ይችሉ የነበረ ይሆናል They just do not want to do it! And want to do the right thing! እንዲህ አይነት ሰዎች፣ ከእንደኔ አይነቱ መደዴ (ordinary person) የሚለዩት፣ በህይወት ምርጫ ነው--ደስታ የሚያገኙበት የህይወት ምርጫ። አለቀ። " በአሜሪካ አገር፣ ተግሪክ ምግብ ቤት ውስጥ፣ ተፈረንጅ ጋር ትከሻ ለትከሻ እየተጋፋ በመብላቱ" ኢትዮጵያ የምትባል ርጉም አገር የምትታየው ሰውም አለ። ይህም የምርጫ ጉዳይ ነው። ይሄ ሰው የተሳሳተው ነገር ቢኖር፣ ኢትዮጵያ ማለት ወንዙ፣ ተራራው፣ አፈሩ... አለመሆኑን ነው። እሱ ግኡዝ ነገር ነው። እኔ አንተ እሱ እሷ ነን ኢትዮጵያ።

... በአለም የመጨረሻው ደስታ የሌለው ህዝብ ነን፣ በአለም የመጨረሻ ድሃ ህዝብ ነን፣ በአለም የመጨረሻ በቂ ህክምና የማያገኝ ህዝብ ነን (መለስ ዜናዊ "ኢትዮጵያ እንዲያውም ዶ/ር አያስፈልጋትም" ያሉትን ልብ ይሏል)፣ በአለም እጅግ በሚያስደነግጥ መጠን ገንዘብ የሚዘረፍባት ሃገር ህዝብ ነን...። በስንቱ ጥሩ ነገር የመጨረሻ ነን? በስንቱስ መጥፎ ነገር የመጀመሪያ ነን? ሃገር ጥሎ በመሰደድ አንደኛ ነን?፣  በውጭ ሃገር ለሚደርስብን ግድያ፣ ግፍ እና በደል የሚደርስልን መንግስት የሌለን ህዝብ ነን፣ በዘረኝነት ፖለቲካ በአለም አንደኛ (ምናልባትም ብቸኛ) አገር ህዝብ ነን። ይህ ሁሉ ችግር እና ስቆቃ፣ በዘር ፖለቲካ እየታሸ ሄዶ ሄዶ፣ ወዴት ነው የሚያመራው? አገሪቱ ብትበታተን እንዴት ነው እያንዳንዱን ሰው አፌክት የሚያደርገው? በውጭ ያለውን *ኢትዮጵያዊ ሁሉ* በቀጥታ አፌክት የማያደርገው ቢሆንም እንኳን፣ የዜግነት፣ ሰብዓዊነት እና/ወይም የሞራሊቲ ጉዳይም ሁሉ ይቀር፣ ደህና። እናት፣ አባት፣ ወንድም፣ እህት፤ወዳጅ፣ ዘመድ፣ ጓደኛ፣ ጎረቤቶች የሉንም? አብዛኛው ከውጭ የሚመጣው ሰው፣ አገሩን የመጨረሻ ማረፊያው/መጦሪያው እንደሚያደርግ ያልማል። ምን አይነት አገር ነው የሚጠብቀው? በእርጅና ወቅት የሚጦሩበት አገር እንዴት ሆኖ እንዲጠብቅ ነው የሚፈለገው?... የመለስ አገዛዝ እድሜ በተራዘመ ቁጥር፣ በዚያው ልክ አበሳችን እየበዛ ነው የሚሄደው። በውጭ ከሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን፣ የሚድያ ድርጅቶቹን በገንዘብ፣ እውቀት፣ ቁሳቁስ እና በሞራል ወዘተ... ለማገዝ ብዙ መስራት ይጠበቃል። ከላይ እንደገለጽኩት፣ በቤተሰብ ደረጃ በመነጋጋር መጀመር ይቻላል።

ቸር ይግጠመን!

ገላነው-ክራር

Gelanew-kirar@hotmail.com